

## 37-2

# እግዚአብሔር ከእኛ ምን ይፈልጋል

ኢሳያስ ጥሪ ሲደርሰው “ከንፈሮቼ ያደፉብኝ መናገር የማልችል ነኝ” አለ (ኢሳ 6፥5)። ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ እንዲመራ እግዚአብሔር ሲጠራው “እኔ ማን ነኝ?” (ዘጸ 3፥11-4፥10-13) አለ። ዮሐንስ የእግዚአብሔር ክብር እንደሚያበራ ጸሐይ ደምቆ ሲያይ፥ “እንደ ሞተ ሰው ሆኖ በእግሩ ሥር ወደቀ” ይላል (ራዕይ 1፥17)። እራሳቸውን የናቁትን እግዚአብሔር አይንቃቸው። ምክንያቱም “ከትሁታን ሰዎች ጋር እገኛለሁ” (ኢሳያስ 57፤15) ስለሚል ነው። ሰው በሕይወቱ “ዝቅ” ማለት የሚችለው፥ በአምላኩ ፊት ራሱን ዝቅ ማድረግ ሲችል ነው። በእግዚአብሔር ፊት ራሱን ዝቅ ማድረግ ያልቻለ ሰው፥ ከሰው ጋር በሚኖረው ግንኙነት እራሱን ዝቅ ማድረግ አይችልም። ማርቲን ሉተር በክርስትያኖች ሕይወት ደምቆ መታየት ያለበት ባህሪ ምንድነው ተብሎ ሲጠየቅ፥ “1ኛ ራስን ዝቅ ማድረግ፣ 2ኛ ራስን ዝቅ ማድረግ፣ 3ኛ ራስን ዝቅ ማድረግ ነው” አለ። “ራስን ዝቅ ማድረግ” ከሁሉም የክርስትና ባህሪያት የላቀ እንዲሆን ያደረገው የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ሁሉ የሚበቅሉበት መልካም መሬት በመሆኑ ነው።

በ16ኛው ክፍለ ዘመን በእውቀታቸውና በቅድስና ሕይወታቸው ይደነቁ ከነበሩት የእምነት አባቶች መካከል ፊለፕ ኔሪ የተባለው ሰው ነበር። አንድ ቀን ፊሊፕ ኔሪን የአገሪቱ ጳጳስ፥ ሮም አጠገብ ከነበረ አንድ ገዳም ሄዶ አንዲት በቅድስና ሕይወቷ የተደነቀች “ቅድስት” ሴት እንዲያይ ጠየቀው። ፊሊፕ ኔሪም ከገዳሙ እንደደረሰ ‘ቅድስት” የተባለችውን ሴት መጥታ እንድታየው መልዕክተኛ ላከባት። ያቺም ሴት ከክፍሉ ስትገባ በጭቃ የተለወሰውን ጫማውን አወልቃ እግሩን እንድታጥበው ጠየቃት። ያቺም ሴት በሁኔታው ተናዳ በኃይለኛ ቃል “እምቢ አላጥብም፤ ማን መሰልኩት! እኔ ነኝ የእርሱን እግር የማጥበው!” በማለት ተናገረች። ፊሊፕ ኔሪም ከገዳሙ ወጥቶ ወደ ሮም ተመለሰ። ለላከውም ጳጳስ “ምንም ቅዱስ ሰው አላገኙሁም፤ ትህትና በሌለበት “ቅድስና” የለም” አለው። ቅዱስ አጉስቲን “ትዕቢት መልዕክ የነበረውን ወደ ሉሲፉርነት እንደለወጠው “ትህትና” ደግሞ ተራውን ሰው ከመላዕክት ደረጃ ያደርሰዋል” አለ።

### “የተቀለበሰ ትህትና” ትህትና አይደለም

“የተቀለበሰ ትህትና” ከላይ ሲታይ “እውነተኛ ትህትና” ይምሰል እንጂ ከውስጡ የተደበቀ ኩራት አለበት። ለምሳሌ፥ “እኔ ፍጹም የማልረባ ነኝ፤ እኔ ከሁሉም የማንስ አነስተኛ ብላቴና ነኝ፤ እኔ አህያ ነኝ፤ ጌታ በእኔ በአህያው ይሠራል፤ ከእኔ ምንም አትጠብቁ፤ እኔ ጥሩ ድምጽ የለኝም፤ ለመስበክ አልተዘጋጀሁም፤ አፍህን ክፈት እኔ እሞላዋለሁ ስላለኝ ብቻ እኔ አፌን እከፍታለሁ፤ እኔ ዝቃጭ አተላ ነኝ፤ ማለት ልማዳዊ የአነጋገር ፈሊጥ እንጂ የእውነተኛ “ትህትና” ሞልክት አይደለም። ይህን ዓይነቱ አነጋገር “ትህትናዬን እዩ” ማለታችን ይመስላል። እንዲህ ዓይነቱ “የተቀለበሰ ኩራት” እንጂ ትህትና አይደለም። ልንሠራ የምንችለውን “አልችልም” የተማርነውንና ያወቅነውን “አላውቅም፤ እኔ ደንቆሮ ነኝ” ማለት “ትህትና” አይደለም። በተፈጥሮ ጌታ ያደለንን ችሎታና ተሰጠ መካድ ትሁት አያሰኘንም። ከንፈር መምጠጥ፣ ጎስቋላ መስሎ መታየት፣ መጨማደድ፣ ተኮራምቶ መቀመጥ፣ ያለንን ልብስ አጥበን በመልበስ ፈንታ ቆሻሾ መታየት እራስን ዝቅ ማድረግ ወይንም ትህትና አይደለም።

### “ትህትና” ምንድነው?

1) “ትህትና” የማይታይ ረቂቅ ነገር አይደለም፤ ወይንም እንደ ልብስ የምናጠልቀውና የምናወልቀው አይደለም። ከእግዚአብሔር የሚሰጠን ሳይሆን፥ እኛ በእግዚአብሔር ፊት የምናሳየው የተሰበረ ልብ ነው። እንዲሁም ሰዎች ሊያዩት የማይችሉት፥ በእግዚአብሔር ፊት ብቻ የምናደርገው (የምናሳየው) አይደለም።

2) “ትህትና” የሚመነጨው ለእግዚአብሔር ጥማት ካለው ልብ ነው። ጥማቱም ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ የተቀራረበ ግንኙነት ለመፍጠር ነው። ያም ሊሆን የሚችለው የራሳችንን ባዶነት፥ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ትልቅነት ስንቀበል ብቻ ነው።

3) “ትህትና” አንዳንድ “ቅዱስ” የሆኑ ሰዎች ብቻ የሚኖራቸው የሕይወት ልምምድ ሳይሆን፥ ማንኛውም አማኝ

ሊኖረው የሚችል የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው። ጳውሎስ "በፍቅር እርስ በርሳችሁ እየተረዳዳችሁ ዘወትር በትህትና፣ በገርነትና በትዕግሥት ኑሩ" (ኤፌሶን 4፥2) በማለት ይመክረናል።

4) "ትህትና" ሰው በሕይወቱ የሆኑለት በጎ ነገሮች ሁሉ ስለበጎነቱ የተደረገለት ሳይሆን፥ ከእግዚአብሔር የተሰጠው እንደሆነ አውቆ ራሱን ዝቅ ሲያደርግ ነው። "ትህትና" ማለት እራስን ዋጋ እንደሌለው መቁጠር ሳይሆን፥ ያለው የተፈጥሮ ችሎታ ሁሉ የራሱ ሳይሆን ከጌታ እንደተቀበለው አውቆ ክብሩን መልሶ ለእርሱ ሲሰጥ ነው።

5) "ትህትና" ካለው ሳይቀንስ ወይንም ሳይበዛ ራስን ሆኖ መገኘት ማለት ነው። የብዙዎቻችን ችግር ከሆነው በላይ በልጠን ወይንም መስለን ለመገኘት መሞከራችን ነው። አንዳንዶች ደግሞ ብርቱዎችና ትጉሆች ቢሆኑም፥ ያንን ይደብቃሉ። ሁለቱም ዓይነት ትክክል አይደለም።

6) "ትህትና" በእግዚአብሔር ላይ ሙሉ በሙሉ እራስን መጣል ማለት ነው። እግዚአብሔር ፈጣሪያችን መሆኑን መገንዘብ ብቻ ሳይሆን መኖራችን የሚወሰነው በእርሱ ብቻ መሆኑን መረዳት ነው።

7) "ትህትና" ከድብብቆሽና ከማስመሰል ሕይወት ነጻ የሚያደርግ መልካም ባህሪ ነው። የማስመሰል ሕይወት ከመምራት እራሱን ነጻ አድርጎ የሚኖር አማኝ ድካሙን ሸፍኖ ከማለፍ ይልቅ ሲደክም "ደከምኩ"፣ ሲስት "ሳትኩ"፣ ሲበድል "በደልኩ" ማለትን ይችላል። ድካማችንና ጉድለታችንን ማሳወቁ በትዕቢት ተይዘን እራሳችንን በማታለል ፋንታ፥ እርዳታ ሲያስፈልገን በወቅቱ እርዳታ እንድንፈልግ ያስችለናል።

## ትንንሽ አማልክት አንሁን

ጀማይካ ውስጥ "እራስ ተፈሪያን" እየተባሉ የሚጠሩ ክፍሎች የጥንቱን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አጼ ኃይለ ሥላሴን እንደ አምላክ ያመልኳቸው ነበር። አንድ ጊዜ አጼ ኃይለ ሥላሴ ጃማይካን ጎብኝተው ሲመለሱ አንድ ጋዜጠኛ "የጃማይካ ሕዝብ እንደ አምላክ ሲያመልክዎ ለምን አይከለክሏቸውም?" ሲል ጠየቃቸው። አጼ ኃይለ ሥላሴም ሲመልሱ "እናክብርህ ሲሉኝ እንዴት አታክብሩኝ እላቸዋለሁ" ሲሉ መልስ ሰጡ። በምንሰጠው አገልግሎት ሰዎች እንዲያከብሩን ብቻ ሳይሆን እንዲያመልኩን የምንፈልግበት ጊዜ አለ። ይህን ዓይነቱ "እራስን ማተለቅ" አደገኛ ነው። የሥነ መለኮት ምሁር የነበረው ጀርመናዊው ባንሆፈር "መመለክ ከሚያደርስ ጠባይ (cultic personality) እንጠንቀቅ፤ ከመመለክ ደረጃ የሚደርሰው አገልጋዩ ባለው ችሎታ ኃይልና ጥበብ ላይ ትኩረት የሰጠ እንደሆነ ነው። ችሎታውና ኃይሉ ሁሉ መልካም ቢሆኑም፥ ያንን አጋኖ ማውራት ግን ሥጋዊ ስለሆነ በክርስትያን ኅብረተሰብ መካከል ሥፍራ የለውም፤ ኅብረተሰቡንም ይመርዛል" አለ። በሐዋርያት ዘመን ጳውሎስና በርናባስ እንደ "አማልክት" መታየት የሚያስችላቸው ዕድል አጋጥሟቸው ነበር። እንደ አጼ ኃይለ ሥላሴ "ግድ የለም ያክብሩን" ብለው ዝም ብለው አልተቀበሉትም። ነገር ግን በሀዘን ልብሳቸውን ቀድደው እየጮሁ "እናንተ ሰዎች ለምን ይህን ታደርጋላችሁ" እኛም እኮ እንደ እናንተ ሰዎች ነን፤" በማለት ከለከሏቸው (የሐዋ. 14፥15)።

"እጄን ስጭንበት ወደቀ፤ እፍ ስልበት መንፈስ ቅዱስን ተቀበለ" በማለት ኢጋነን የምናወራ ወይንም ወንጌልን ከመስበክ ይልቅ እነዚህን በመሳሰሉ ነገሮች ላይ ብቻ ትኩረት የምንሰጥ ከሆነ፥ በአንዳንዶች ዘንድ ከመደነቅ አልፈን እንደ ትናንሽ "አማልክቶች" እንታያለን። ክሪሶስተም የተባለው ጸሐፊ "አንዳንድ አገልጋዮች የሚኖሩት ከሰዎች በሚደረግላቸው ጭብጨባ ብቻ ነው፤ ከተጨበጨበላቸው መንግሥተ ሰማይ የገቡ፣ ካልተጨበጨበላቸው ደግሞ ሲኦል የወረዱ ይመስላቸዋል" አለ። ብዙ ጊዜ "የክብር ፍለጋ" ጥማት በሌሎች ሕይወት እንጂ በእኛ ሕይወት ውስጥ እንዳለ አይታየንም። ሲ ኤስ ሉወስ "ከስህተታችን ሁሉ የሚበልጠው ትዕቢት በውስጣችን አለመኖሩን አለማወቃችን ነው። በእኛ ውስጥ መኖሩን ባወቅን ቁጥር በሌሎች ላይ ስናየው ከቀድሞ ይልቅ ይበልጥ እንጠላዋለን" አለ።

## ትሁት መታረምን አይጠላም

"ነገር ግን እኔ አሁን የሆንሁትን የሆንሁት በእግዚአብሄር ጸጋ ነው፤ የተሰጠኝም ጸጋ ያለ ፍሬ አልቀረም" (1 ቆሮ 15፥10) ሲል እኔን አታመስግኑኝ በውስጤ የሠራውን ጌታ አመስግኑ ማለቱ ነው። አማኞች በራሳቸው ትምክህት ውስጥ እንዳይኖሩ ያስጠነቅቅ የነበረው ጳውሎስ ብቻ ሳይሆን፥ ሙሴም በዘመኑ ለነበሩት የእሥራኤል ሕዝብ ይመክር ነበር (ዘዳ 8፥17-18)። በእግዚአብሔር ፊት ራሱን ዝቅ ማደግ የሚችል ሰው በሰውም ፊት ራሱን ዝቅ ማድረግ ይችላል። አጰሎስ የተማረ ቅዱሳት መጽሕፍትን ጠንቀቆ የተማረና ጥሩ የአነጋገር ችሎታ ያለው ሰው ነበር። ይሁን እንጂ አንድ ጉድለት ነበረበት። ይኸውም ከዮሐንስ ጥምቀት በስተቀር ሌላ አያውቅም ነበር። "እርሱ በድፍረት በምኩራብ መናገር ጀመረ፤ ነገር ግን ጵርሲላና አቂላ በሰሙት ጊዜ ወደ ቤታቸው ወሰዱትና የእግዚአብሔርን መንገድ ከፊት ይልቅ በትክክል አብራርተው ገለጡለት" ይላል (የሐዋ 18፥26)። አጰሎስ "እንዴት እኔ ከእነርሱ እማራለሁ" በማለት ትምህርታቸውን አልተቃወመም።

ጴጥሮስ ወደ አንጾኪያ ሲመጣ ከአህዛብ ጋር ስለ መብላት የነበረው አቋም ጳውሎስን ደስ ስላላሰኘው ገሰጸው። ጳውሎስ ከጴጥሮስ በክርስትስና ሕይወቱ ልጅ ቢሆንም፥ ጴጥሮስ "ለምን ተገሰጽኩ" በማለት ቅር አላለውም። ቅሬታ እንዳልነበረው የምናየው ጴጥሮስ በጻፈው መልዕክቱ ነው (2 ጴጥሮስ 3፥15)። ጴጥሮስ "ሁላችሁም ትህትናን እንደ ልብስ ለብሳችሁ አንዱ ሌላውን ያገልግል፤ ምክያቱም እግዚአብሔር ትቢተኞችን ይቃወማል ለትሁቶች ግን ጸጋን ይሰጣል" ይላል ( 1 ጴጥሮስ 5፥5)። ጴጥሮስ ሲገሰጽ "እኔ ትልቅ ነኝ፤ ግሳጼን አልፈልግም" አላለም። እግዚአብሔር "ኩራትን" ይጠላል (ምሳሌ 6፥16-19) ትሁቶች እንድንሆን ይፈልጋል።

.................................................................................

**በሚቀጥለው ክፍል እስክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**